ሰኔ 16 ቀን 2003 ዓ.ም. “ሕዝብ ወደፊት ይወስናል?” በሚል በጻፍኩት ጽሁፍ ታዋቂው የስነ ጽሁፍ ሰው ኃይሉ (ገሞራው) በአንዳንድ አስተያየት ሰጪዎች ገሞራው እንደጻፈ ተወስዶ መዘለፉ ስለተሰማኝ የኃይሉ (ገሞራውን) ግጥሞችና ሥራዎች ለማስታወስ

## ገሞራው :- ሀገሩን የከዳ ሀገርም አይኑረው (ከአሉላ)

ገሞራው…ገ…ሞ…ራ…ው. . .
ስምህ ነው ገሞራው
ገ…ሞ…ራ…ው… ነው ስምህ
ምሳሌህ ምንድን ነው
ያንት ስብህናህ?

እሳት ነው ገ…ሞ…ራ…ው…
ገ…ሞ…ራ…ው… ነው እሳት
ተሟልቶ የተካነው
የሕይወት አንደበት
ብዕር ነው ገ…ሞ…ራ…ው…
ገ…ሞ…ራ…ው… ነው ብዕር
እግዜር የባረከው
ኢትዮጵያዊ በዘር።

አፃፃፍ ቅላጼው - አንደበት ሲነዝር
ተነቦ አይጠገብ - የገሞራው ብዕር
ተደምጦ ወኔ ነው - የገሞራው ግጥም
ስብህናን ወስዶ - በስሜት ሚያሰጥም::

ነጐድጓድ ገ…ሞ…ራ…ው…
ገ…ሞ…ራ…ው ነጐድጓድ
በረከተ ብሎ
መርገምን ሲያወርድ
ብዕሩን ካነሳ - እጁን አርጎ ሰደድ
እንዴት ይመግባል - ለወዳጅ ለዘመድ
እንጠሮጠስ ይከታል - ጠላትን አርጎ አመድ።

እናንተ ከንቱዎች - ባገርላይ አትምጡ
እኔ አላማረኝም - ምክሬን አድምጡ
ዋላ ከውደቁ - በገሞራው እጅ
እኔን አያድርገኝ - ከሃዲ አጎብዳጅ
ጦር ነው አንደበቱ - በምፄ ለመጣ
መብረቅ ያውርድበት - እሱ አያቅም ጣጣ
ይጮሃል ገሞራው - አንደበቱን ላጣ።

EthioLion.Com

ጎርፍ ነው ገ…ሞ…ራ…ው…
ገ…ሞ…ራ…ው… ነው ጎርፍ

ማንበልበል ከጀመረ - በብሩህ አንደበቱ
ለሀገር ለወገን - አቤት ማስደሰቱ።
የገሞራው ብዕር ዓለምን ይቃኛል
ይናወጣል ፍጡር - ምድርም ያገሳል
ነጎድጓድ ያጅባል - ማዕበል ያስነሳል
የተኛውን ሁላ ይቀሰቅሰዋል
ወኔው የሸናውን ያንከባልለዋል
እንደ ደራሽ ውኃ ይጠራርገዋል
እንጠሮጦስ ብሎ ገደል ይከተዋል።

በናቴኮ ሴት ነኝ - ገሞራው ይለናል
ማን ወንድ ተገኝቶ - ይቀናቀነዋል
ብዕሩን አንስቶ - ይሞግትላታል።

እናትክን አልኩልህ - ገሞራው ደስ ይብልህ
ወቶ አዳሪ መሆኑ - አንተን ምን አስቀናህ
ዓባይ እንዳይወይን - ይኸው ሰደብኩልህ።

ገ…ሞ…ራ…ው…ገሞራው
አንት ጀግና ደብተራ
ድቁናውን ትተህ ስትሆን ያገር አውራ
መርገጫ ብታጣ በረሀ እንዳሞራ
ከየት ነው ያለኸው ልይ እስቲ ተጣራ።

የት አለ ያ ደብተራ - ፍሬው የጎመራ
ገና መች ተነካ - አለበት አደራ
ሀገር ስትታመስ - ፍዳውን ሕዝብ ሲያይ
እየሸነሸነ ሲጥላት ከፋፋይ
በሀገር የመጣ ይታለፋል ወይ?
መሸሽግ አይሆንም ብቅ በል ካደባባይ
ብዕርህ ብርታት ነው ለሀገርም ሲሳይ።

እሳትም ከሆነ ገሞራው ይፈንዳ
እየሳቀ ያንደው ይህን ምድረ ባንዳ
ብዕርህን ተኩስ ገና አለብህ ዕዳ
አነጣጥረህ ምታው ከቶም እንዳትለቀው
ሀገሩን የከዳ ሀገርም አይኑረው።

አሉላ (alulla2@yahoo.com) ሰኔ 20 ቀን 2003 ዓ.ም. ተፃፈ